መጋቢት 4/2003

# በኖርዌይ የኢትዮጵያ ስደተኞች ችግርን በተመለከተ ኢሕአፓ ተንቀሳቀሰ

በኖርዌይ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን የጥገኝነት መብት መሰረዝ ብቻ ሳይሆን ከስራ ቦታ በማፈናቀልና አልፎም ወደ ኢትዮጵያ በግድ ለመመለስ የኖርዌይ መንግስት የጀመረውን ህገ ወጥና ጎጂ እንቅስቃሴ በመቃወም ስደተኞቹ ራሳቸው የተቃውሞ እንቅ ስቃሴያሰሙ መሆናቸው ቢታወቅም ኢሕአፓ ይህን ጥረት በመደገፍ ከዚህ በፊት ያደርግ እንደነበረው ሁሉ ዛሬም እንቅስቃሴውን ቀጥሏል።

በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታው ፓርቲ (ኢሕአፓ) የአመራር ኮሚቴ አባል አቶ ኢያሱ ዓለማየሁና የዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት (አኢሴድ) የአመራር ኮሚቴ አባል የሆኑት ወይዘሮ ገነት ግርማ በኦስሎ ከተማ ከየካቲት 29 እስከ መጋቢት 4 ተገኝተው የኖርዌይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተጠሪዎችን፣የፖለቲካ ድርጅት ተወካዮችን፣ የኢሚግሬሽን ጉዳይ ሀላፊዎችንና ስደተኛ ወገኖቻችንን ወዘተ በሰፊው አነጋግረዋል። ወገኖ ቻችን በኖርዌይ ኢፍትሀዊ እርምጃ እየተሰቃዩ መሆናቸውንና በተለይም ሴቶች ስደተኞችና የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎችን በተመለከተ ህገ ወጡ ወሳኔና እርምጃ እያደረሰ ያለውን ጉዳ ትና ጭንቀት በማንሳት ጥብቅ ተቃውሞ ለባለስልጣኖቹ ደርሷል። የኖርዌይ መንግስት መለስን አግባብቶ ስደተኞችንሲመለሱ እንዲቀበሉ የኖርዌይ ጠቅላይ ሚኒስቴር በቅርቡ አዲስ አበባን ጎብኝቶ ያደረገው ጥረትም አሳፋሪ መሆኑ ለባለስልጣኖቹ ተነግሮአቸዋል። በኖ ርዌይ ባለፈው ዓመት የስደተኛ መብት የጠየቁ ኢትዮጵያውያን ቁጥርም 500 ያልደረሰ ሲሆን ከዚህ በላይ ለሆኑ ኤርትራውያን፣ ሶማሊዎች ወዘተ ግን ኖርዌይ ጥገኝነት መስጠቷም ተነስቷል። ኖርዌይ ኢትዮጵያውያንን በብሄረሰብ በመሸንሸን ኦሮሞና ከኦጋዴን ነኝ ያላለውን ጥገኝነት መከልከሏንም ኢሕአፓ አጥብቆ አውግዟል። በኖርዌይ ያሉ ኢትዮጵያውያን ስደተ ኞች ሁኔታቸው አሳሳቢ በመሆኑም በዓለም አቀፍ ደረጃ ኢትዮጵያውያን ሙሉ ደጋፋቸውን እንዲሰጧቸው ኢሕአፓ ጠርቷል። በተለይም ሴት ወገኖቻችን እየተጠቁ ስለሆነ በአኢሴድ የተጀመረውን ተቃውሞናለሴቶቹ ድጋፍ ማጠናከር አስፈላጊ መሆኑም ጫና ተሰጥቶታል። የስደተኞችን ጥያቄ ለማደፍረስና ለማርከስ የሚራወጡት ወያኔዎችና ሀላፊነት የጎደላቸው ክፍሎችም ተወግዘዋል።